የረቡዕ ታህሳሥ 5 1998 ዓም (ዲሴምበር 14 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## የሞራል ሥልጣን የማን ነው?

በአለፈው ሳምንት በአንድ ድረ ገፅ አማካኝነት ወያኔ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን የስም ዝርዝር አውጥቶ በብሔራዊ ክህድትና በአሸባሪነት ወንጀል የሚፈለጉ መሆናቸውን በመግለፅ ይፋ አድርጓል። ቀደም ሲል ካወጣው የ 58 ዜጎች ክስ ዝርዝር በተጨማሪ መሆኑ ነው። መለስ ዜናዊ ከእነኝህ ኢትዮጵያውያንን መሀል አንዳንዶቹን ምናልባት በአካል ከአገኛቸውም በቀጥታ ወደ ወኅኒ ቤት በመወርወር የሞት ፍርድ አስፈርዶ ወዲያውኑ ቅጣታቸውን በተግባር ለመተርጎም እንደማይመለስ የሁሉም ግምት ሆኗል። ወይም ደግሞ እንደ ለመደው በየቦታው ገዳይ ቡድን በመላክ የማስገደል ሙከራ ያደርግም ይሆናል። ሌላም ሌላ የማስፈራሪያ ርምጃ ሊወስድም ይችላል። የሚፈራለት ካገኘ ማለታችን ነው። በዚህ ብሔራዊ ክህደት ተከስሰው፥ ስማቸው ከተዘረዘረው መካከል፥ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ያላቸው ታማኝነትና ያበረከቱትም ብሔራዊ አገልግሎት የአንድ ትውልድ ዘመን ያስቆጠረና በትግሉ ሜዳም ቢሆን በመስዋዕት የታጀበ የአያሌ ዘመን አኩሪ ተመክሮአቸውን በቆራጥነት ያስመሰከሩ ይገኙበታል። ጥቂቶቹም፥ በአሁኑ ወቅት የወያኔን ብሔራዊ ጥፋት በመኮነን የሚታገሉ ናቸው። ሌሎች ደግሞ አፍቅሮ ወያኔነታቸው ቢታወቅም ለማደናገር የተደበላቁ ናቸው። ይህ የሰሞኑ የስም ዝርዝር ውንጀላ በሀገር ውስጥ የሚካሄደው ወከባና አፈና ቅጥያ ነው እንጅ ከዚያ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ። የዚህ ሐተታ ዓይነተኛ ዓላማ፥ መለስ ዜናዊንና እነዚህን ለሀገራቸው ነፃነት የሚታገሉትን ዜጎች ማንነትና ምንነት ለማወዳደር አይለም። ይህን ማድረግ ማለት ለከሀዲው መለስ ዜናዊ ክብርና መድረክ መስጠት ማለት ይሆናል። እናም ይህን አናደርግም።

ይህች ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘወትር የምፀትና የታሪክ እንቆቅልሽ ተፈራራቂ ሰለባ መሆኗ ግን ሁል ጊዜ ዜጎቿን ሲያበሳጭም ሲያስገርምም ሲያስከፋም የቆየ ጉዳይ ሆኗል። የምፀትና እንቆቅልሽ መፈራረቅ በአንድ ኅብረተስብ ዘንድ የሚያስከትለውን አንደምታና አስተጋብዖ በቅጡ ለመገንዘብ፥ የዚህ ክስተት ከደረሰበት ዜጋ የበለጠ ሊያውቀው የሚችል የለም። ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ እነዚህ ክስተቶች ሲፈራረቁባት ቆይተዋል። ይህ ፍርደ ገምድል ክስተትና ሂደት በሀገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ በተፈራረቁት ሦስት መንግሥታትና ሥርዓት ውስጥ መልኩን እየለዋወጠ ሲመጣና ሲሄድ ቆይቷል። አርበኞቹ እንደ ሀገር ሻጭ፥ ከሃዲ ባንዳዎቹ ደግሞ እንደ ታማኞች ሆነው ሲቆጠሩ ቆይተዋል። በላይ ዘለቀና ታከለ ወልደ ሐዋርያት የመሳሰሉ አርበኞችና ለሀገራቸው ሚኞች፥ በንጉሡ ዘንድ ስላልተወደዱ እንደ ከሃዲ ሲቆጠሩ፥ ከጣሊያን ፋሽስት ጋር ሲተባበሩ የነበሩት ባንዶች ግን የሥርዓቱ ተባባሪና ቁንጮ በመሆናቸው ብቻ ሲሞካሹ ነበር። መንግሥቱ ኃይለ

ማርያምን የተቃወመው ሁሉ÷ እንደ ሀገር ሻጭ እየተቆጠረ ሲጨፈጨፍ÷ እንደቆየ ለሁሉም የቅርብ ትዝታ ነበር፡፡ መለስ ዜናዊም ዛሬ በበኩሉ÷ ይህንኑ እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ግንዛቤ እንዳለ ቢሆንም÷ መንግሥትና ሥርዓት በመፈራረቅ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የሚፈፅሙት የማያቋርጥ በደል ጭቋና÷ ምፀትና እንቆቅልሽ ግን ሊቆም የሚገባው ነው ብለን ለማመን እንፈልጋለን፡፡ ወያኔ ከነሥርዓቱ በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ የሚፈፅመውን በደልና ግፍ ማስቆም መቻል አለብን፡፡ ኅብረተሰቡ ምፀትና እንቆቅልሽ ሲፈራረቅበት በአርምሞ ሊመለከትው ይገባል ከሚሉት ክፍሎች አይደለንም፡፡ አጥፊውን ከአልሚው÷ ባንዳውን ከአርበኛው÷ ከሀዲውን ከታማኙ÷ ውሸታሙን ከሀቀኛው÷ ቀጣፊውን ከጨዋው አሾክሿኪዉን ከኩሩው መለየትና ፍርድ መስጠት የኅብረተሰቡ ኃላፊነትና ግዴታ ነው፡፡ እነዚህ ዘረኞችና አጥፊዎች በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የሚፈፀሙትን የአካልና የመንፈስ ሰቆቃ ለአንዴም ለሁሌም ማስወገድ መቻል ይዋል ይደር የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡

እረ ለመሆኑ በአሁኑ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በብሔራዊ ክህደት ሊከሰስና ሊቀጣ የሚችል ማን ነው? በአሸባሪነትስ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው ማን ነው? በዚህ የፍርድ ሸንጎ÷ ማን ተከሳሽ? ማንስ ከሳሽ? ማንስ ዳኛና ጠበቃ ሊሆን ይችላል? በፍርዱ ሸንጎ በታዛቢነቱ ወንበር ማን ይሰየማል? ለዘመናት አብሮ በአንድ ላይ የተቀመጠን ሕዝብ ከሁለት የከፈለ÷ ያጋጨ ማን ሆኖ ነው? የኢትዮጵያን ታሪክና ህልውና የተፈታተነ ማን ነው? የሐገራችንን ታሪካዊና የብሔራዊ ነፃነታችን ምልክት የሆነችውን ሰንደቅ ዓላማችንን ማን ነው ብጣሽ ጨርቅ ብሎ ያዋረዳት የተመጻደቀባት? ለዘመናት አብረው መኖር ብቻ ሳይሆን÷ የባዕድንን ወረራ ሁሉ በጋራ በመመከት የጋራ ሀገራቸውን ነፃነት በጋራ አስከብረው የቆዩትን ኢትዮጵያውያን ዜጎች በብሔራቸው÷ በቋንቋቸውና በሃይማኖታቸው ከፋፍሎ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር÷ ሕዝቧንም እንደ ሕዝብ ለማጥፋት እየተጣደፈ ያለው ማን ይሆን? የኢትዮጵያን ሕዝብ የነፃነት ልዕልና ለባዕዳን አሳልፎ የሰጠ መለስ ዜናዊ አይደለምን? ታዲያ ይህንን ታላቅ ብሔራዊ ክህደትና ወንጀል የፈፀመ ግለሰብ ÷ ምን የሞራል ሥልጣንና ሰብዕና ኖሮት ነው ሌሎቹን ንፁሃን ዜጎች በሀገር ክህደት የሚከስሰው?

በእርግጥ ይህ የመለስ ዜናዊ የሰሞኑ የሀገር ክህደት የክስ ድራማ ማንም ኢትዮጵያዊ ከቁም ነገር ይቆጥረዋል አይባልም፡፡ እራሱ መለስና ተባባሪዎቹም ቢሆኑ የወንጀሉ ክስ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይ ያገኝልናል ብለው ያምኑበታል ለማለት አይቻልም፡፡ መለስ ዜናዊ በአሁኑ ወቅት÷ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያንን ስም ዝርዝር በማውጣት በሀገር ክህደት ወንጀል ይፈለጋሉ ብሎ ማለቱ÷ ምናልባት አራት ዓላማዎችን ይመታልኛል ብሎ በመመኘት ይመስላል፡፡

1) አሁን ከገባበት የፖሊቲካ ውጥረት ማስተንፈሻ ለማግኘት ሲል የዕለታዊ ፕሮፓጋንዳ ከበሮ ለመምታት ብቻ ነው:: በዚህ ሳቢያ የሕዝቡን የትግል አቅጣጫ ያሳተም ያስለወጠም ይመስለዋል::

2) በቆራጥነት የሚታገለውን ክፍል ለማስፈራራትና ለማስጠንቀቅ የጣረው ከንቱ ሙከራ ነው::  ምናልባት የሚፈራ ካገኝ ይሰራልኛል ብሎም ያስብ ይሆናል::

3) በሀገር ክህደትና ሕዝብን ለአመፅ ማነሳሳት ብሎ መፈረጁ፥ ባዕዳን አለቆቹን አሸባሪዎችን እየተዋጋሁ ነው ብሎ  ለማለትና ድጋፋቸውን እንዳያጓድሉበት የዘየደው ከንቱ ጥረት ነው::

4) ወደፊት ተቃውሞ በመነሳት ለመታገል ያቀደውን ክፍል አስቀድሞ ቅስም ለመስበርና  አንገት ለማስደፋት ብሎም፥ የቅድሚያ ማጥቃት ዘመቻ ሙከራ ለማድረግ ነው::

አራቱም ሙከራዎች  በፈለገው መንገድ ቢያገለባብጣቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አቅጣጫ የሚያስቱ አይሆኑም::  ከሀዲው መለስ ዜናዊ አስቀድሞ ሌሎቹን ከሃዲ ናቸው ብሎ  በመክሰስ የራሱን ወንጀል ለመደበቅ መከጀሉም፥ ዉሃ የሚቋጥር መላ አልሆነለትም:: ደርግና ተባባሪዎቹ ትላንት ብዙሃኑን ኢትዮጵያውያን/ያት አስቀድመው አድሃርያን ብለው በመፈረጅ ቢጨፈጭፏቸውም፥ እናም፥ እራሳቸውን ተራማጅ ለማስመሰል ያደረጉት ሙከራም ከወንጀል ተጠያቂነት አላዳናቸውም:: ከታሪክና ከትውልድ ተወቃሽነትና ተከሳሽነት ሊድኑ አልቻሉም:: የዛሬዎቹም ወያኔዎች የደርግን ፈለግ ተከትለው ንፁኃንን ዜጎች በሀገር ክህደትና በሕዝብ አበጣባጭነት ለመወንጀል ቢጥሩም፥ እራሳቸው ከወንጀላቸው ነፃ ሊሆን አይችሉም :: አንዱ ሌላውን ለመወንጀል፥ ወንጃዩ አስቀድሞ የሞራል  ሥልጣንና የሰብዕና ልዕልና ሊኖረው ይገባል::  በሀገራችን ታሪክና ባኅልም ይሁን በኅብረተሰባችንም ፍርድ፥ እንዲሁም በህግ ሽንጎ፥ ሌላውን መወንጀልና ስም ማጥፋት፥ በራስ ላይ የሞት ቅጣት እንደ መፍረድ መሆኑን መታወቅ አለበት::  በኋላ ማጣፊያውም ይቸግራል:: ጊዜ አጋጥሞኛል ብሎ  የራስን ወንጀልና  ብሔራዊ ክህደት ባልሰሩ ሰዎች ላይ ለመላከክ መሞከር፥ ታሪክና ጊዜ ሲዋሃዱ የሚበይኑት የፍርድ ብያኔ ይሆናል::  ይህንን ክስተት ያልተገነዘቡ ክፍሎች አስቀድመው ሁለት ጊዜ እንዲያስቡ ያስፈልጋቸዋል::  ይገባቸዋል:: መካሪም ያሻቸዋል:: ::

እውነተኛዎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቁርጥ ቀን ልጆች ፥ ማንነታቸውን ቆራጥ መስዋዕትን በጠየቀ ትግል ስላስመሰከሩ፥ የመለስ ዜናዊ ማስፈራራትና የክስ  ወንጀል የሚበግራቸው አለመሆኑን ወዳጅም ይሁን ጠላት ሊያጤነው ይገባል:: ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአመፅ ትግል አጋርና ብቁ መሪ ገና ባይኖረውም፥ መነሻው በፅኑ አለት ላይ  ስለተመሠረተ፥ማንም ኃይል ሊያጠፋው አልቻለም:: ወደ ፊትም ቢሆን ሊያጠፋው የሚችል ኃይል አይኖርም:: ባጭር ጊዜ ውስጥ ግቡን ለመምታት ካስፈለገ ግን፥ አንድ

ዓይነተኛ ኃይል ያስፈልገዋል፡፡ ይኸውም በብሔራዊ ዓላማና ስትራተጂያዊ ራዕይ ላይ የተገነባ አመራር ሰጭ መሪ ድርጅት ነው፡፡ ይኽ ከሌለ፥ የሕዝቡ የትግል ፍጻሜ ብዙ ጊዜ ከመውሰድ የሚያድነው አይገኝም፡፡ ወያኔን በአጭር ጊዜ ለማንበርከክ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አቀነባብሮ የሚመራው መሪ ድርጅት መኖር ወቅታዊና አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ በብሔር አቀፍ ደረጃ፥ ማለትም ዘርና ሃይማኖት፥ ፆታና ዕድሜ፥ የሙያና የትምህርት፥ የገጠርና የከተማ፥ የነጋዴና የአርሷ-አደር ልዩነት ሳያደርግ ሁሉ አቀፍና ዘርፈ-ብዙ ትግል ማካሄድ የወቅቱ ቀዳማይ አጀንዳ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የትግል ስልትን የመምረጥና የማቀናጀት ጉዳይ ከባድ አይሆንም፡፡ ይህ ሁኔታ እንዳይከሰት ነው ዛሬ፥ ወያኔና ባዕዳን አለቆቹ ታጥቀው የሚሰሩት፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ግማሾቹ ታስረዋል፡፡ ሌሎች ተገድለዋል፡፡ በርካታዎቹም የገቡበት አልታወቀም፡፡ አንዳንዶቹም የተጣለባቸውን የሕዝብ አደራ በመርገጥ ከወያኔ ጋር ተባብረዋል፡፡ ያም ሆኖ ግን፥ ማንም ኃይል ሊበግረው ያልቻለ የሕዝብ የአመፅ ትግል እሳተ ገሞራውን አርግዞ ይገኛል፡፡ ይኸም በመሆኑ፥ መለስና ግብረ-አበሮቹ እንደ ቆሰለ አውሬ እየተቅበዘበዙ ናቸው፡፡ የተወሰኑትን ዜጎች በሀገር ክደት ወንጀልና በአሸባሪነት ለመፈረጅ የሚፍጨረጨሩት፥ የሚይዙት የሚጨብጡት ከማጣት ነው፡፡ የወያኔ መሪዎች የተበጠሰውን የሥልጣናቸውን ገመድ ለመቀጠል የብድር ህይወትና ኑሮ ፍለጋ በመማሰን ላይ ናቸው፡፡ ትንሽ ምዕራፍም ቢሆን ለመጓዝ ካስቻላቸው፥ የማይፈነቅሉት የተንኮል ድንጋይ አይኖራቸውም፡፡ በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት የተወሰኑ ዜጎችን ስም ዝርዝር በማውጣት በወንጀል ይፈለጋሉ ብሎ ማወጅ፥ ከዚህ ከመርበትበትና የሚሰሩትን ከማጣትና ቅጥ-አምባር ከመጥፋት የመነጨ የዳበሳ ጎዞ ነው፡፡ ማነኛውንም ዜጋ፥ ምንም ምን ይሁን፥ ምንም ዓይነት ያለፈ ህይወት ይኑረው አይኑረው፥ ወይም ማነኛውንም ድርጊት ይፈጽም አይፈጽም፥ የወያኔ መሪዎች፥ ቢያንስ በሀገር ክህደት ለመወንጀል፥ የሞራል ሥልጣንም ይሁን የሰብዕና ብቃት የላቸውም፡፡ የሞራል ሥልጣንም ይሁን ብሔራዊ ኃላፊነትና ችሎታ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው፡፡

የሌባ ዓይነ ደረቅ እንዲሉ የመለስ አገዛዝ በሀገርና በህዝብ ላይ ክህደትን ፈፅሞ እያለ ለሀገር የሚታገሉትን በተገላቢጦሽ በክህደት ሊከስ መቃጣቱ ምንኛ ሀፍረት ቢስ እንደሆነ ዳግም ከማሳየት ሌላ ዋጋ ቢስ ነው፡፡ ቆርጦ የተነሳን ህዝብ የጨቋኝ ድንፋታ የሚገታው አይሆንም፡፡